ብልፅግና ፓርቲ
PROSPERITY PARTY

# የብልጽግና ፓርቲ የአደረጃጀትና የአሠራር መመሪያ (ረቂቅ)

# 1. የመመሪያው መሻሻል አስፈላጊነት

1. “ከቃል እስከ ባህል” በሚል መሪ ቃል በተካሄደው የብልጽግና ፓርቲ 2ኛው መደበኛ ጉባዔ የጸደቀው መተዳደሪያ ደንብ በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲ አካላት ተግባራዊ የሚሆኑ አዳዲስ ድንጋጌዎች እና ትርጓሜዎች የተደነገጉ በመሆናቸው መመሪያውን ከተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ ጋር ማነበብ ዋንኛውና አንደኛው ምክንያት ነው፡፡
2. በአንደኛ ጉባዔ በጸደቀውም ይሁን በሁለተኛ ጉባዔ በተሻሻለው የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መመሪያዎች ተዘጋጅተው በሚመለከተው አካል ጸድቀው ሥራ ላይ መዋል እንዳለባቸው ይደነግጋሉ፡፡ በዚህ መሠረት የብልጽግና ፓርቲ የአባላትና የአመራር አካላት አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር ጊዜያዊ መመሪያ የካቲት 2012 ዓ.ም. ጀምሮ ላለፉት 5 ዓመታት ሳይጸድቅ በጊዜያዊነት መቆየቱ አግባብ አለመሆኑን የብልጽግና የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን በ2016 ዓ.ም. በፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ባካሄደው ኢንስፔክሽን ለአደረጃጀት ዘርፉ እና ለዋና ጽ/ቤት ለሚመለከተው አካል ቀርቦ እንዲጸድቅ ምክረ-ሃሳብ ማቅረቡ ሁለተኛው ምክንያት ሆኗል፡፡
3. መመሪያው በሥራ ላይ በዋለባቸው ዓመታት ውስጥ በሥራ ውስጥ የታዩ እና በተለያዩ ጊዜያት በተካሄዱ ሱፐርቪዥኖች ግልጽነት የሚጎድላቸው እና በመመሪያው ያልተሻፈኑ ጉዳዮች(ለአብነት ትርጉም፣ የዋና ጽ/ቤት ዘርፎች አደረጃጀት፣ የፌዴራል ተቋማት አደረጃጀት፣ በፓርቲ አካላት መካከል የሚኖር የግንኙነት ሥርዓት፣ የስብሰባ መደበኛ የግንኙነት ጊዜ እና ግንዛቤ ስለመፍጠር) መኖራቸው በመረጋገጡ መመሪያውን ለመሻሻል ሦስተኛ ምክንያት ነው፡፡
4. ሌላው መመሪያው ከሕግ አዘጋጃጀት አኳያ ሲታይ የይዘትና የቅርጽ ክፍተቶች ያሉበት በመሆኑ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እንደ አራተኛው ምክንያት ተወስዷል፡፡

## 2. የመተዳደሪያ ደንብ አዳዲስ ድንጋጌዎች

1. **በአንቀጽ 2 ስር ትርጓሜ የተሰጣቸው በርካታ አዳዲስ ቃለቶችና ሐረጎች መኖራቸው፣**
2. **በአንቀጽ 8(4)(ቀ)** - ሁሉም የፓርቲ እጩ እና ሙሉ አባላትና አመራር በብልፅግና ቤተሰብ እና በብልፅግና ህብረት አደረጃጀቶች ተደራጅተው የመንቀሳቀስ እንዳለባቸው፣
3. **አንቀጽ 11(6)** - ዕጩ የሆነው አባል የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ እና የፓርቲውን የዲሲፕሊን መመሪያ አውቆ ከተቀበለ በኋላ በአባላት ኮንፈረንስ ፊት ቃለ መሃላ ይፈጽማል።
4. **አንቀጽ 15(1)** ማንኛውም የፓርቲ አባል እና አመራር በሚመለከተው የፓርቲ አካል የወጣ የዲሲፕሊን መመሪያ/ዎችን የማክበር ግዴታ አለበት*(መመሪያ ቁጥር 12/2015)*።
5. **አንቀጽ 28(3)** - የብልፅግና ህብረት ኮንፈረንስ በየ3 ወሩ የሚካሄድ ሆኖ የብልፅግና ቤተሰብ ውይይት በየወሩ ይካሄዳል።
6. **አንቀጽ 29(1) -የፓርቲ ኮንፈረንስ ተግባርና ኃላፊነት** - በየደረጃው የፓርቲው ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል።
7. **አንቀጽ 30(6) (ሐ)- የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ** - የፓርቲ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣሉ፣
8. **አንቀጽ 31(4) (በ) የየደረጃው ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች** የፓርቲ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች በስራ ላይ ያውላሉ፣ ለአባላትና ለአመራር ግንዛቤ ይፈጥራሉ፣ መከበራቸውን ይከታተላሉ።

## 3. የጊዜያዊ መመሪያ(የካቲት 2012) ክፍተቶች

1. መመሪያው የቃላትና ሐረጎች ትርጓሜ የሌለው መሆኑ፣
2. በአንቀጽ 2 እና 3 ተግባራዊ ያልሆነ የፌደራል ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት ያካተተ በመሆኑ፣
3. በአንቀጽ 6(14) የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለፓርቲው ፕሬዝዳንት ይሆናል በሚል በተሻሻለው የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 14(1) (2) (ለ) እና አንቀጽ 26(2) ጋር በሚጋጭ መልኩ የተቀመጠ በመሆኑ፣
4. በአንቀጽ 88(7) (8) የፌዴራል ተቋማት አደረጃጀት የተንዛዛ አደረጃጀት፣ ግልጽ ተግባራትና ኃላፊነትና አሠራር ያልተዘረጋለት በመሆኑ እና
5. የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ከክልሎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሥራ አመራር ኮሚቴ ጋር እና በየደረጃው የሚገኙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በተዋረድ የሚገናኙበት አሠራር አለመኖሩ ዋና ዋናዎች ናቸው፡፡

## 4. የተሻሻለው የአደረጃጀትና አሠራር መመሪያ አዳዲስ ጉዳዮች

1. በአንቀጽ 2 ትርጓሜ ተቀምጧል፣
2. በአንቀጽ 7፣ 8 እና 11 የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ እና የዋና ጽ/ቤቱ የሥራ አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት፣ ተግባራትና ኃላፊነት እና አሠራር በግልጽ ተደንግጓል፣
3. በአንቀት 7(3) በየደረጃው ለሚገኙ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ተግባራትና ኃላፊነቶች ተደንግጓል፣
4. በአንቀጽ 10(5) የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት እና የክልል ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ በየሦስት ወሩ በእቅድ አፈጻጸም ግምገማ የጋራ የውይይት መድረክ ያካሂዳሉ።
5. በአንቀጽ 11(3) በዋና ጽ/ቤት ስር ለተደራጁ ዘርፎች የተሰጡ ተግባራትና ኃላፊነቶች እንደአስፈላጊነቱ በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ስር ለተደራጁ ዘርፎችም ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።
6. በአንቀጽ 11(4)(መ) ዘርፎች በየደረጃው የሚገኙ ተመሳሳይ ዘርፎች ጋር በየሶስት ወሩ የእቅድ አፈጻጸም ግምገማ የጋራ የውይይት መድረክ ያካሄዳሉ።
7. በአንቀጽ 12—20 የፌዴራል ተቋማት አደረጃጀት፣ ተግባራትና አሠራር ተዘርዝሯል፣
8. በአንቀፅ 68 በየክልል የሚገኙ የፌዴራል መንግስት ተቋማት አባላት አደረጃጀት በግልጽ ተደንግጓል።

# አመሠግናለሁ!